የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

# በንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት

# ዕቅድ ላይ የተሰጠ ግብረ- መልስ

ሕዳር/2014 ዓ.ም

## መግቢያ

የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 54 መሠረት በየአምስት ዓመቱ በሚደረግ ሀገር አቀፍ ምርጫ የሚመሰረት ከፍተኛ የመንግስት የስልጣን አካል ሲሆን ም/ቤቱ በሕገ-መንግስቱ የተሰጠውን ሕግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ አካላትን የመከታተልና የመቆጣጠር፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን ለማከናወን እንዲሁም የሕዝብ ውክልና ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ለማድረግ በም/ቤቱ የአሠራርና የአባላት የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 መሠረት የም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ፣ አፈጉባኤ፣ ም/አፈ ጉባኤ፣ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ በም/ቤቱ ውስጥ መቀመጫ ያላቸው የፓርቲ ተጠሪዎች አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

6ኛውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ አዲስ ምክር ቤት በመመስረቱ አሁን ያለውን የመንግስት አደረጃጀትና የትኩረት አቅጣጫ መነሻ በማድረግ ምክር ቤቱ ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በውሳኔ ቁጥር 3/2014 11 ቋሚ ኮሚቴዎችን ያደራጀ ሲሆን የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም በዚህ መሠረት መቋቋሙ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሚከታተላቸው ተቋማት ውስጥ አንዱ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው። በዚሁ መሠረት የ2014 በጀት ዓመት የተቋሙን ዕቅድ በዝርዝር በማየት ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በመለየት እንዲሁም ለቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በማካተት የሚከተለው ግብረ መልስ ተሰጥቷል።

## በጥንካሬ የታዩ

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ አሠራርና የግብይት ሥርዓትን ለማስፈን፣ በዕሴት ጭማሪ የላቀ የውጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ለማሰደግና እና የዓለም አቀፍ አካባቢያዊ ትስስር የሚያጎለብቱ የንግድ ስምምነቶችን በማጠናከር የገቢያ መዳረሻዎችን ለማስፋት የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ማቀዱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገራችን የንግድ ሥራ አመቺነት (Ease of Doing Business) ደረጃን ለማሻሻል የንግድ አመቺነት ውጤቱን (DB Score) አሁን ካለው 48 ወደ

80 ነጥብ ከፍ በማድረግ በ2022 ዓ.ም ከምርጥ 50 ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ማቀዱ፣

- ሀገራችን የአለም ንግድ አባል ለመሆን የምታደረገውን ሂደት የተጎተተና የተራዘመ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ የድርድር ሰነዶችን አጠናክሮ ለማቅረብ መታቀዱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሁን ያለውን የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት ሪፎርም በማድረግ እና የንግድ ተወዳዳሪነትን በማስፈን የሸማቹን ህብረተሰብ እርካታ 100% ለማድረስ መታቀዱ፣
- በአምራች ኢንዱስትሪዎች በሀገር ዉስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የተሳለጠ የምርት ግብዓት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራታቸዉና ደህነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፤የጥራትና ሪጉላቶሪ ቁጥጥር ሥራዎች፣ ካሊቤሬሽን አገልግሎት፣ የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት፣ የጥራት መሠረት መዋቀር ተቋማት ብቃትና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ መታቀዱ፣
- የኤክስፖርት ምርቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት፣ ተግባራዊ የተደረጉ የኤክስፖርት ማበረታቻ ስርዓትን ውጤታማነትን ማረጋገጥ እና አዳዲስ ሥርዓቶችን በጥናት ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱ፣
- አዳዲስ የግብርና ምርቶችን ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ማስገባት፣ የኤክስፖርት ምርት ማሳያ ማዕከላትን የመገንባት፣ የማስተዳደርና ማስተላለፍ እና ንግድ ግኑኝነትና ድርድሮችን ለሀገሪቱ ምርቶች መዳረሻዎችን በሚያሰፋ መልኩ ማካሄድ፣ እንዲሁም የሀገሪቱ ምርት በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ለምርቶቻችን አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ መታቀዱ፣
- በኮሜሳና ሌሎች የአከባቢያዊ የንግድ ውህደቶች ተሳትፎን ለማሳደግ መታቀዱ፣
- የምርቶችን ጥራትና የመለኪያ መሳሪዎቸዎችን ትክክለኛነት ባረጋገጥ የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት እና የገበያ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ መታቀዱ፣
- አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ የአስራር ስርዓት መዘርጋት፣ አሰፈጻሚ አካላት ለማስተባበር መታቀዱ፣
- የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት የዓለም ንግድ ድርጅትና ቀጠናዊ የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለማጠናከር ጥናትና ምርምሮችን ለማካሄድ መታቀዱ እንዲሁም የገበያ ሰንሰለትን በማሳጠር የገበያ ትስስር በመፍጠር ተወዳዳሪነትና ህጋዊነት ለማጠናከር ጥናት ለማድረግ መታቀዱ፣

- ሃገራዊ የጥራት መሠረት ልማቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ለማመንጨት የሚያግዙ ጥናትና ምርምሮችን ለማካሄድ መታቀዱ፡፡

## በእጥረት የታዩ

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀጠናዊ ትስስር አንጻሩ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖረንን የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ጉዳይ በስፋት የሚያካትት በመሆኑ ራሱን ችሎ እንደ አንድ የትኩረት መስክ ታሳቢ ተደርጎ በእቅዱ አለመካተቱ፣
- ሀገራችን በውጭና በዉስጥ በጦርነት በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚዉና በዲፕሎማሲው ፈርጀ ብዙ ጦርነት ውስጥ እንዳለች የሚታወቅ መሆኑና ዕቅዱ የኢኮኖሚውን ዘርፍ ለማሸነፍ የሚያስችል ዕቅድ መሆኑ እንደሚኖርበትና ነገር ግን የኢኮኖሚውን ጦርነት ለማሸነፍ በዕቅዱ አለመካተቱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የገበያ ሥርዓት የሚያግዝ የገበያ መረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በዕቅዱ አለመካተቱ፣
- በሥራ ላይ ያሉ የሕግ ማዕቀፎችና የማስፈጸሚያ ማንዋሎች በመፈተሽ አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ እንዲሁም ውድድርን የሚገድቡ አሠራሮችንና ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በማጥናት ጠንካራ የገበያ ውድድር ለማስፈን የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ሊያሰረ የሚያስችል በዕቅዱ አለመካተቱ፣
- አገልግሎት አሰጣጡ ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን በማዉረድ ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር በጉልህ በዕቅዱ ዉስጥ አለመካተቱ
- የጥራት መሠረተ ልማትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተቋማትን በማደራጀት የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለማስጠበቅና የኢኮኖሚውን የልማት ስትራቴጂ የሚያግዙ ስታንዳርዶች በማዘጋጀትና በትግበራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና የብሔራዊ ሥነ ልክ ላቦራቶሪ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ለማሳደግ የአለካክ ወሰኖችን የሚያረጋግጥ አሰራር በአግባቡ ያልተመላከተ መሆኑ፣
- የሰው ኃይሉን የመፈጸምና የማስፈጸም እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በየደረጃው ማጎልበት፣ የለውጥና ሪፎርም ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን የአስተዳደርና የአሰራር ስርዓቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሠራርን በተጠናከረ መልኩ አለመታቀዱ፣

- ሚ/ር መ/ቤቱ የዋጋ ንረትን ፣ጥቁር ገበያና ሌሎች የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚጎዱ ህገ ወጥ ተግባራትን የሚቀጣጠርበትን የቢዝነስ ሴኩሪት በቴክኖሎጂ የታገዘ በእቅዱ አመካተቱ
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን የዓለም አቀፍ አክሬዲቴሽን ፎረም ስምምነቶችን በመፈረም አባል ሆኖ የተመዘገበ ቢሆንም በአዳዲስ የአለካክ መስኮች ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት በመስክ፣ በሚዛን አለካክ፣ በተንቀሳቃሽ ካሊብሬሽን ላብራቶሪ፣ በይዘት፣ በግዝፈት፣ በግፊትና በሙቀት አለካክ መስክ ዓለም አቀፍ የዕውቅና ሠርቲፊኬት የሚያስገኝ በዕቅዱ አለመቀመጡ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሳለጠ ሀገራዊ የገበያ ማዕከላት ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመነጋገር የገበያ ማዕከላትን ባለመገንባቱ ምክንያት የዋጋ ንረት፣ የምርት ስርጭትና አቅርቦት እንዲሁም የማስተዋወቅ ስራዎችን በአግባቡ መስራት የሚያስችል በእቅዱ አለማካተቱ፣
- የንግዱ ማህበረሰብ እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖረው በማድረግና በነጻ ለመደራጀትና ከመደራጀት በሚገኘው ጥቅም ላይ ትኩረት እንዲሰጥ መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል። ሰፊ የውድድር መንፈስ በመፍጠር በማምረትም ሆነ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሁሉ በውድድር ብቻ የጋራ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን ሊቀይር የሚችል ድምፅ ማሰማት የሚችልበት አሰራር አለመኖሩ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጥራት ፖሊሲ በተመለከተ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር አብሮ በመስራት የተለያዩ ጥናቶችንና ምርምሮችን ለማድረግ የሚያስችል የትኩረት አቅጣጫ የሚያመላክት በእቅዱ ዉስጥ ያላመላከተ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግብይቱን በኦን ላይን /Online/ ከማድረግ አንጻር፣ ሲስተምን መሰረት ያደረገ የአሰራር ስልት፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት የሚያስችል እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ ግንዛቤ የመፍጠርና አቅምን ከማጎልበት አንጻር በእቅዱ የተካተተ በቂ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጭ ገበያን ከማፈላለግ አንጻር ለውጥ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ቁጥጥር ከማድረግ ባሻገር በማምረት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ የምርት ጥራት ችግሮችን ለመቅረፍ በቅንጅት ከሚመለከተው አስፈጻሚ አካላት ጋር ለመስራት በእቅዱ ዉስጥ አለመካተቱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ የፍጆታ ሸቀጦች በህብረተሰቡ ውስጥ አከርካሪ ሆኖ የሚነሳና የዋጋ ንረቱ ዋና መነሻ እንደመሆኑ መጠን ይህን ችግር ከመሰረቱ

ለመፍታት የሚያችል ከሚመለከታቸው አካላትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ያመላከተ ቢሆንም ከችግሩ አንገብጋብና አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ለመስራት የሚያችል በሚገባ ያላመላከተ መሆኑ፣

- በሀገራችን በርካታ ህብረተሰብ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ቢሆንም የንግዱ መረብ ውስጥ ያልገቡ፣ ለመንግስት መክፈል የሚገባውን የማይከፍሉ ብዙ ነጋዴዎች እንዳለ ይታወቃል፡፡ በተመሳሳይ ምርት እያለ የሚፈጠረውን እጥረት እንዴት መፍታት እንዳለበትና ምርቶቹ ጥራታቸውን እንዲጠቢቁ ከማድረግ አኳያ የክትትልና ቁጥጥር ስልቶችን የዕቅዱ አካል አለማድረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጦርነት ውስጥ ያሉ ክልሎችን በተመለከተ የወደሙ ንብረቶችና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት የሚያችል እንዴ አንድ የመፍትሔ አቅጣጫ በዕቅዱ ውስጥ ያላመላከተ መሆኑ፣
- ከዉጪ ንግድ ምርቶች ጋር በተያያዘ እንደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ስለዘመናዊ የግብይት ስርዓት፣ ስለ ምርቶች ጥራት ስለ ገበያ መረጃና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ጉዳዮች፣ ለአምራች ህብረት ስራ ማህበራት እና የንግድ ሥራን ለሚመሩ፣ የአሰራር ስርዓት ሰራተኞች የሚሰጡ የግንዛቤ መፍጠሪያ በግባብ በዕቅዱ አለመካተቱ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪውን የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን እና ጥራት ላይ ያለው ግንዛቤ ከአምራቹ ጋር ብቻ ሳይሆን ከባለሙያውም ጋር ያለዉ ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ፣ ይህንን ለመቅረፍ የሚያስችል የአሰራር ስልት በአግባቡ በዕቅዱ አለመቀረጹ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህግ ማዕቀፍን በተመለከተ ደረጃ ያልወጣለትን ምርት ደረጃውን ላልተገባው ምርት የመጠቀም አምራቾች በህግ አግባብ ተጠያቂ የሚሆኑበት ስልት በአግባቡ በዕቅዱ ውስጥ ያልተመላከተ መሆኑ፣
- ውስብስብ የዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓትና ህጎችና ባሉት የንግድ ሕጎች ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- አምራቾች የኤክስፖርት ምርቶቻቸውን በጥራትና በብዛት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማምረትና ለማቅረብ የሚያስችል እና አምራቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና ለብዝበዛ እንዳይጋለጡ የሚያደርግ የገበያ ሰንሰለትና ግንዛቤ የሚያገኙበት ቀላል የአሰራርና ዘዴ በዕቅዱ ያለመካተቱ፣
- ከተሰጡባቸው የንግድ ሥራ ፈቃድ መስኮችና አላማዎች ውጪ መነገድ ወይም መስራት፣ በኮንትረባንድና በህገ-ወጥ ንግድ አማካኝነት ወደ ገበያ የሚገቡ

የአስገዳጅ ምርቶች በየጊዜው እየጨመረ መምጣት እና ያለ ደረሰኝ ግብይት የሚከናወኑ እንዲሁም የነጋዴዎች አድራሻ በአግባቡ ተለይቶ የማይታወቅ በመሆኑ የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተገቢው ሁኔታ ለመጠበቅ የሚያስችል አሰራር በአግባቡ በዕቅዱ አልተከተተም፣

- የዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ማለትም ሴቶችን ወደ አመራርነት በማምጣቱ፣ ኤች አይቪ ኤድስ በደማቸው ውስጥ የምገኝ ሰራተኞችና በአይቪ.ኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት ለመደገፍና እንዲሁም የአየር ብክለትን ለመከላከል በዕቅዱ አለመካተቱ፡፡

## በዕቅዱ ለቀጣይ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀጠናዊ ትስስርን የዓለም አቀፍና አህጉራ አቀፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ታሳቢ ያደረገ እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ አደርጎ በዕቅዱ ማስቀመጥ ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅዱ የጥራት ፖሊሲ አለመኖሩ በግልጽ ያመላከተ ቢሆንም የንግድ ስርዓቱን ለማዘመን የተሻለ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ምቹ ለማድረግ አኳያ ለቀጣይ ትኩረት ተደርጎበት ሊሰራበት ይገባል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሀገራችን የሚያገኘውን የውጪ ምንዛሪ የሚጨምርና የሀገር ውስጥ ገቢ ምርቶችን የመተካትና የምርት አቅርቦትንና ጥራት ከፍ በማድረግ ሀገራችን የምትፈልገውን ኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕግ ማዕቀፍ ደረጃ ያልወጣለትን ምርት ደረጃውን ላልተገባው ምርት የመጠቀሙ አምራቾች በሕግ አግባብ ተጠያቂ የሚሆኑበት ስልት በአግባቡ በዕቅዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የገበያ ሥርዓት የሚያግዝ የገበያ መረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን በዕቅዱ ማካተት ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሳለጠ ሀገራዊ የገበያ ማዕከላት ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመነጋገር የገበያ ማዕከላትን ባለመገንባቱ ምክንያት የዋጋ ንረት፣ የምርት ስርጭትና አቅርቦት እንዲሁም የማስተዋወቅ ስራዎችን በአግባቡ መስራት የሚያስችል በዕቅዱ ማካተት ይገባል፣
- አምራቾች የኤክስፖርት ምርቶቻቸውን በጥራትና በብዛት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማምረትና ለማቅረብ የሚያስችል እና አምራቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና ለብዝበዛ እንዳይጋለጡ የሚያደርግ የገበያ አሰራርና ሰንሰለት

እንዲሁም ግንዛቤ የሚያገኙበት ቀላል የአሰራርና ዘዴ በዕቅዱ ሊያካትት ይኖርበታል፣

- ሀገራችን በውጭና በውስጥ በጦርነት በፖለቲከው፣ በኢኮኖሚውና በዲፕሎማሲው ፈርጀ ብዙ ጦርነት ውስጥ እንዳለች የሚታወቅ መሆኑና ዕቅዱ የኢኮኖሚውን ጦርነት ዘርፍ ለማሸነፍ የሚያስችል እንደአንድ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይኖርበታል፣
- በዓለም ላይ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ ያለው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ያጋጠመውን የኢኮኖሚ ስብራት ለማከም የሀገር ውስጥ ምርቶች ከባለፈው የበለጠ በመጨመር የአገራችንን ኢኮኖሚ ለመታደግ የሚያስችሉ ስልቶችን መቅረጽ ይኖርበታል፣
- የጥራት መሠረተ ልማትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተቋማትን በማደራጀት የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለማስጠበቅና የኢኮኖሚውን የልማት ስትራቴጂ የሚያግዙ ስታንዳርዶች በማዘጋጀትና በትግበራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና የብሔራዊ ሥነ ልክ ላብራቶሪ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ለማሳደግ የአለካክ ወሰኖችን የሚያረጋግጥ አሰራር በአግባቡ መቅረጽ ይኖርበታል፣
- አምራቾችና ሸማቾች ከእጅ በእጅ ግብይት ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግብይት እንዲሁም የወደፊት ውል ግብይት(Forward Trading) እድገት ሽግግር ላይ መሆኑን ያገናዘበ ቀጣይነት ያለው የሰው ሃይል(TechnicalCapability) አቅም ግንባታ ክፍተቶችን ለሟሟላት ጥረት ማድረግ አለበት፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ባሉ ማዕከላት የኤሌክትሮኒክስ ግብይት ተሳታፊዎችን ሊያበረታታ የሚችል የዕውቅና ወይም የዕድሳት መስፈርት ማሻሻያ እንዲሁም የክህሎት ስልጠና ክፍተቶችን ለይቶ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅቱን የመጠነ የአደረጃጀት እና የአሰራር ማሻሻያ ጉድለት፣ ተሞክሮን የመቀመርና የማስፋፋት ባህል ማስቀመጥ ይኖርበታል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የዕቅዱ አካል አድርጐ መስራት ይኖርበታል (ማለትም ከኤች አይቪ ኤድስ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ አካል ጉዳተኞች ለመርዳት፣ .... ወዘተ

## ማጠቃለያ

ቋሚ ኮሚቴው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅት በጥልቀት የገመገመ ሲሆን በጥንካሬና በድክመት በመለየት በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ጥንካሬዎችን በማጐልበት፣ ድክመንቶችን በማረም፣ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ የተቀመጡና በዕቅዱ ያልተካተቱትን በማካተት ትኩረት በመስጠት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ ዕቅዱን በማዳበር የተሟላ የ2014 ዕቅድ በማድረግ ወደ ተግባር በመግባት ውጤታማ ስራ መሰራት ይኖርበታል የሚል ግብረ-መልስ ተሰቷል፡፡